# እንዳትቀየሙኝ

ከአይሳነው እሱ

ይኸ ሰው ታመመ…ሆነ ያልጋ ቁራኛ፣

ከፉ ምች መታው…ተጠጋው መጋኛ፣

በሽታው ሥር ሰዶም…የማይድን ሆነና፣

አረፈ ይኸው ዛሬ…ሄደ ትናንትና፣

ሲባል ባገራችን…ሲነገረን መርዶ፣

ደረት እየደቁ…መቅበር ሙሾ አውርዶ፣

ነበር ልማዳችን…ከሌሎች መለያ፣

ምነው የትናንቱ…ዛሬ አልሆነ ታድያ?

እንዲህ የትናንቱ…ዛሬን እያጠፋ፣

እንዲህ ዘመነኛው…ያረገ እየገፋ፣

ወገን በወገኑ…በራሱ እየከፋ፣

እንዴት ይዘለቃል…ኑሮ ያለተስፋ?

ደስታው ሁሉ ኀዘን…ኀዘኑም ደስታ፣

ምን ይሉ እንቆቅልሽ…ምን ይሉ ጨዋታ?

ሰው "አባቱ" ሲሞት…ዘለላ እንባ ካጣ፣

"ቁንጮው" ፍግም ሲል…ዳንስና ዝነጣ፣

ካማረው እስክስታ…ከሆነ ብስጩ፣

መመርመር ያሻዋል…የጭካኔው ምንጩ።

እነዛሬ እንግደል…እነዛሬ እንዝረፍ፣

እነዛሬ እንብላው…እነዛሬ እንቀርጥፍ፣

ትናንትም ብቸኛ…ዛሬም ራሳችሁ፣

መቼም አትማሩም…ኑሩ ለሆዳችሁ።

በሰፈራችሁት…ቁና ተሰፈሩ፣

ዛሬም ብቻችሁን…ነገም ብቻ ቅሩ።

ጊዜው ደረሰና…ይኸው ታዘብኳችሁ፣

ሕዝባችን ምትሉት…አንድም ሰው የላችሁ።

ደጉን ወገን ክፉ…ለሟን ሀገር ጥፉ፣

ላደረጋችሁት ከፍተኛ “ውለታ”

ካምላክ እጅ አገኙት…የሱ ነው ችሮታ።

“ነፍስ ይማር” ነበረ…ያገር ባሕል ወጉ፣

የጭካኔያችሁ ጦር…መዘዙ፡ ሰበቁ፣

ካዘናችሁ ድንኳን…ከመርዶው እንዳልደርስ፣

ያገር ባሕልና…ወግ ልማድ እንዳፈርስ፣

አድርጎኛልና…እንዳትቀየሙኝ፣

ድንጋይ ስለጠፋ..ምሸከመው ቋጥኝ፣

“ሃገር” ላዬ ጭኜ…እማጸናለሁኝ፣

“ወገን” እባካችሁ እንዳትቀየሙኝ።

አይቀሬ ነውና…መቀጠሉ ህይወት፣

የወገኔንና ያገሬን…አንድነት፣

በጋራ ጠብቀን…ሃገር ሰላም ወርዶ፣

“ነፍስ ይማር” እላለሁ…ተስፋ አልቆርጥም ከቶ።

ዘረኝነት ሥሩ…ተነቅሎ ተንዶ፣

እኩል ሆነን ነጻ…ባገር ፀሐይ ወጥቶ፣

ሰንደቁ አርማዩ…የታየ ለት ጎልቶ፣

"ነፍስ ይማር" እላለሁ…ተስፋ አልቆርጥም ከቶ።

ቁስሌ አልሻረም ገና…አነከሳለሁኝ፣

በወጋኝ ጦራችሁ…እሰቃያለሁኝ፣

ካዘናችሁ ድንኳን…ከመርዶው እንዳልደርስ፣

ያገር ባሕልና…ወግ ልማድ እንዳፈርስ፣

አድርጎኛልና…እንዳትቀየሙኝ፣

ድንጋይ ስለጠፋ…ምሽከመው ቋጥኝ፣

"ሃገር" ላዩ ጭኜ…እማጸናለሁኝ፣

"ወገን" እባካችሁ…እንዳትቀየሙኝ።

ከአይሳነው እሱ

ነሐሴ 2004